

በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር

የንግድ የመንገድ የሕዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተር አደረጃጀት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥና የስምሪት የአፈፃፀም መመሪያ ማብራሪያ

ጥር 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

1. መግቢያ

ትራንስፖርት ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እድገት ፋይዳው የጎላ ከመሆኑም ባሻገር ድንበር-የለሽና የማያቋርጥ እንቅስቃሴ ያለው የአገልግሎት ዓይነት ነው፡፡ ሀገራችን ለጀመረችው የብልፅግና ጉዞ እና የሪፎርም ዕቅድ ከማሳካት አኳያ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ለውጦችን መሠረት ያደረገ ሁለንተናዊ የለውጥ ትግበራ መኖር እንዳለበት ይታመናል፡፡ ለዚህ ደግሞ የትራንስፖርት አገልግሎት መሻሻል ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቁልፍ እድገቶች እንዲሻሻሉ የማይተካ ሚና አለው፡፡ ዘርፉ ለሀገራዊ ዕድገት የሚኖረው ጠቀሜታ ሰፊ በመሆኑ ልዩ ትኩረት ሊሰጠውና በተገቢ ሕጎች እና አሰራሮች ሊመራ ይገባል፡፡ በመሆኑም እስካሁን በሀገራችን ያለው የትራንስፖርት አገልግሎት ዕድገት እያሳየ ቢሆንም መንግሥት ይህንኑ ሁኔታ በመገንዘብ የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎችን እያከናወነ ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ በአገልግሎት ዕርካታ እንዲያገኝና አገልገሎት ሰጪውም ለሚሰጠው አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችል አሠራር በመዘርጋት ላይ ይገኛል፡፡ በሀገራችን እየተሰጠ ያለው የንግድ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ዘላቂነት ያለውና የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ፣ ኢንቨስትመንትንና ጤናማ ውድድርን የሚያበረታታ፣ የሕዝቡን የመክፈል አቅም ያገናዘበና አቅርቦትን የሚያሳድግ ወጥ የሆነ አሠራርን የሚከተል ሆኖ እንዲከናወን ኦፕሬተሮችን በዘመናዊ አደረጃጀት፣ አሠራርና በሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲጠናከሩ በማድረግ መከናወን ይኖርበታል፡፡

በመሆኑም ቀደም ብሎ በስራ ላይ የነበረው የፌደራል ትራንፖርት ባለስልጣን በአዲሱ የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት ፈርሶ ከትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር እንዲወሀድ በመደረጉ፤ በአዲሱ የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 መሰረት ጠንካራ አቅም ያላቸው የንግድ ድርጅቶች ለመፍጠር በማለም በአዋጅ ቁጥር 468/1997 ተቋቁመው በስራ ላይ የነበሩ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት አደረጃጀት እንዲፈርሱ በመደረጉ እንዲሁም ነባሩ የህዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት የአደረጃጀት እና የስምሪት አፈጻጸም መመሪያ በርካታ ችግሮች የተስተዋለበት በመሆኑ የሕዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተር የአደረጃጀት፣ ብቃት ማረጋገጫና የስምሪት አፈፃፀም መመሪያን ማሻሻል አስፈልጓል፡፡

በዚሁም መሰረት በሀገር አቋራጭ እና በዓለም-አቀፍ የንግድ የመንገድ የህዝብ ማመላለሻ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ኦፕሬተሮች ውስጣዊ አሠራራቸውን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በማጠናከር የተሸከርካሪዎች ስምሪት በቴክኖሎጂ የታገዘና በዘርፉ ባለሙያ የሰው ኃይል የሚመራበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 12(2) መሠረት ይህ የንግድ የመንገድ የሕዝብ ትራንስፖርት የኦፕሬተር አደረጃጀት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ እና የስምሪት አፈፃፀም መመሪያ ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል፡፡

2. **<u>መመሪያውን በማሻሻል ማሳካት የተፈለገው ዓላማ</u>**

በህዝብ ትራንስፖርት ዘርፍ የተሠማሩ ኦፕሬተሮች የሥራ ብቃታቸውንና የአደረጃጀት ጥንካሬያቸውን መሠረት ያደረገ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡

- ግልጽ የአደረጃጀት ሥርዓት በመዘርጋት በቴክኖሎጂ የታገዘ፣ ጠንካራና ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥና የቁጥጥር ሥርዓትን የሚከተሉ የሕዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተሮችን ማፍራት፤
- በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችን በማበረታታትና በመደገፍ ተወዳዳሪ ሆነው የሚቀጥሉበትን፣ አዳዲስ ባለሀብቶችም ወደ ዘርፉ የሚገቡበትን ሁኔታ በማመቻቸት የአገልግሎቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ፤
- የዘርፉ ኦፕሬተሮች አሠራር፣ ብቃትና አደረጃጀት ሀገራችን በሚኖራት አህጉራዊ፣ ቀጠናዊ እና የሁለትዮሽ የመንገድ ትራንስፖርት ትስስር ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- በዘርፉ ከፍተኛ አቅምና ብቃት ያላቸውን ኦፕሬተሮች በፍጠር በመካከላቸው ያለውን ውድድር ከፍ ማድረግና የተቀናጀ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት በመዘርጋት የጎበረተሰቡን የመክፈል አቅም ባገናዘበ መልኩ እንዲጓጓዙ ማስቻል ነው፡፡

3. **<u>የአደረጃጀት መመሪያውን ማሻሻል ያስፈለገበት ዋና ዋና ምክንያቶች</u>**

- የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጥባቸው በሀገር ውስጥ እና በዓለም-አቀፍ መነሻና መዳረሻ ቦታዎች ላይ በቋሚነት ሲሰጥ የቆየው መደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት የስምሪት አገልግሎት፤ የፍሬንቻይዝ መስመሮች የስምሪት አገልግሎትና የመናኸሪያ

አገልግሎት አስተዳደር አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ከመጣው የሕዝብ የአገልግሎት ፍላጎት አኳያና እየተገነቡ ካሉ ዘመናዊ መናኸሪያዎች ጋር የማይጣጣም መሆኑ፤

- እስካሁን በስራ ላይ ያለው የደረጃ አሰጣጥ ላለፉት ስምንት አመታት ሲሰራበት የቆየ ሲሆን አሁን ወቅቱ ከደረሰበት ቴክኖሎጂ ጋር የተጣጣመ እንዲሆንና፤ በዘርፉ ላይ እስካሁን ያን ያህል የጎላ ለውጥ ያልታየበትና አሁንም በዘርፉ ላይ በርካታ ዓመታትን ያስቆጠሩና ለአገልግሎት አሰጣጥ ምቹ ያልሆኑ፤ ለትራፊክ አደጋ ተጋላጭ የሆኑና የአየር ብክለትን በማስከተል ረገድ የጎላ ድርሻ ያላቸው ተሽከርካሪዎች በመኖራቸው፤
- በስራ ላይ ያለው አደረጃጀት የተበጣጠሰ፤ ለውጥ ሊያመጣና ተወዳዳሪነትን የሚያበረታታ ባለመሆኑ፤የተጠናከረ አደረጃጀት በመፍጠር በዘርፉ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ካለመቻሉም ባሻገር ለበርካታ ውስብስብ ችግሮች መንስኤ መሆን መቻሉ፤
- ነባሩ አደረጃጀት በክልሎች በወጥነት እየተተገበረ ባለመሆኑና የተሻለ መግባባትን በመፍጠር በሁሉም አካባቢ ተመሳሳይ የህዝብ ትራንስፖርት አደረጃጀት እንዲፈጠር ማድረግ በማስፈለጉ፤
- የኦፕሬተር ፈቃድ ለመውሰድ የሚጠየቀው በየደረጃው የተቀመጠው የተሽከርካሪ ቁጥር ብዙ በመሆኑ፣ መመሪያው የንግድ ተቋማትን የገበያ ድርሻ የማያበረታታ እና ወደ ዘርፉ ለመግባት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ በዘርፉ የሚገቡ ባለሀብቶችን የማያበረታታ በመሆኑ፤
- በዘርፉ የተሰማሩ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት ውጤታማ ባለመሆናቸው መንግስት እነዚህን ማህበራት ወደ ንግድ ተቋም መሸጋገር እንዳለባቸው አዲስ በወጣው የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ የተደነገገ በመሆኑ ከአዋጁ ጋር የሚጣጣም አደረጃጀት በማስፈለጉ፤
- የሀገራችን የህዝብ ትራንስፖርት አገልሎት የሚሰጡ ኦፕሬተሮች ከጎረቤት ሀገራትና አህጉር ከሚገኙ ትራንስፖርተሮች ጋር ተወዳዳሪና ተመጋጋቢ እንዲሆኑ ለማስቻል፤
- ሀገራችን አባል በሆነችበት የምስራቅ እና ደቡባዊ አፍሪካ ሀገራት የሶስትዮሽ ትራንስፖርት እና ትራንዚት ፋሲሊቴሽን ፕሮግራም ላይ ሀገራቱ በትራንስፖርት ዘርፍ የሕጎች፣ የአሰራር እና የሲስተም ወጥነት /Harmonazation of laws, Standards and Systems/ እንደሚተገብሩ በመርህ ደረጃ ያስቀመጠ ሲሆን አሁን በስራ ላይ ያለው መመሪያ ሲፈተሽ በቀጣይ በሚተገበረው በዚህ የትራንስፖርት ትስስር ሊያሰራ ባለመቻሉ፤

- አደረጃጀቱም ሆነ የተሸከርካሪዎች ስምሪት አሰጣጡ በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ በመሆኑ የተሸከርካሪዎችን ወቅታዊ መረጃ/Real Time Information/ የማያሳይ በመሆኑ ይህም በተለያዩ ጊዜያት በተለይም የህዝብ እንቅስቃሴ ከፍተኛ በሚሆንበት ሰዓት ለአፈጻጸም አስቸጋሪ ሲያደርገው ቆይቷል፡፡

  - አሁን ሀገራችን አላል በሆነችበት የሶስትዮሽ ቀጠናዊ ትስስር ውስጥ አሁን ያሉትን የህዝብ ማመላለሻ ማጎበራትን እና ድርጅቶችን አቅማቸው እና አሰራራቸው በኢንቨስትመንት ፖሊሲ ላይ የተቀመጠውን ውጤት ሊያመጡ እንደማይችሉ የተደረገው ጥናት በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡
  - የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ኦፕሬተሮች ላይ ተፈጻሚ የሆኑ አንድ አይነት ዓላማ ያላቸው በርካታ መመሪያዎች በመኖራቸው እና ሳይሻሩ ለረዥም አመታት በመቆየታቸው ለአፈጻጸም ከፍተኛ ተግዳሮች በመፍጠሩ፤
  - በአጠቃላይ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የስምሪት አሰጣጥንና የመናኸሪያ አስተዳደርን በማሻሻል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን በማድረግ ነባር መመሪያዎችን ለማሻሻል መነሻ የሚሆን ሰነድ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡ በየመናኸሪያዎቹ የስምሪት አገልግሎት የሚሰጥባቸው መመሪያዎች ረዥም ጊዜ ያገለገሉና ብዙ ክፍተት የሚስተዋልባቸው በመሆናቸው በአጠቃላይ የስምሪት አሰጣጡ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የፈጠረ በመሆኑና መናኸሪያዎችም እየተዳደሩበት ያለው አሠራር ግልፅነት የጎደለውና ብዙ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በስፋት የሚስተዋሉበት በመሆኑ እነዚህን የኦፕሬተር ፈቃድ አሰጣጥ እና የስምሪት አፈጻጸም መመሪያዎች በመሻር አዲስ መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

4. **<u>የመመሪያው ዝግጅት</u>**

ከላይ በተጠቀሱት ዋና ዋና ምክንያቶች መመሪያውን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የተለያዩ ሀገሮችን ተሞክሮ በመፈተሽ እና በነባሮቹ መመሪያዎች ላይ በተግባር ወቅት ሲያጋጥም የነበረውን ችግር በማጥናት የማሻሻያ ረቂቅ መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን በረቂቅ መመሪያው ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በተፈጠሩ መድረኮች ላይ ውይይት ተደርጎበት በተሰጡ አስተያየቶች እንዲዳብር ተደርጓል፡፡

እንዲሁም አዲስ በወጣው የፌዴራል አስተዳደር ስነ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 የአስፈጻሚ አካላት መመሪያ ሲያወጡ ሊከተሏቸው የሚገባቸውን ሂደቶች መሰረት

በማድረግ ረቂቅ መመሪያውን ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ በማሳተምና በተቋሙም ድረ-ገጽ ላይ በመጫን አስተያየቶችን በጽሑፍ በመሰብሰብ እና የተሰጡ አስተያየቶች መካተት ያለባቸውን በረቂቅ መመሪያው ላይ በማካተት ለረቂቅ መመሪያው ግብዓት ተደርገዋል፡፡

5. <u>የመመሪያው ዋና ዋና ይዘት</u>

1) ክፍል አንድ - ጠቅላላ ድንጋጌ
   - አጭር ርዕስ
   - ትርጓሜ
   - ዓላማ
   - የተፈጻሚነት ወሰን
2) ክፍል ሁለት - ስለኦፕሬተር የወል ድንጋጌዎች
   - ስለ ኦፕሬተሩ ግዴታዎች
3) ክፍል ሶስት - የአደረጃጀት እና የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች
   - የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች፤
   - የኦፕሬተር ፈቃድ አሰጣጥ፤
   - የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ደረጃዎች እና አይነቶች
   - ለሁሉም ዓይነት ኦፕሬተሮች የተቀመጠ ዝቅተኛ መስፈርት
   - የህዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች የአገልግሎት ወሰን
   - የሰው ኃይል አደረጃጀት
   - የደረጃ ማሻሻያ እና ክለሳ
4) ክፍል አራት- የሕዝብ ትራንስፖርት ስምሪት አፈጻጸም እና ቁጥጥር ሥርዓት
   - የሕዝብ ትራንስፖርት ስምሪት አፈጻጸም
   - የልዩ ጉዞ ስምሪት አገልግሎት አሰጣጥ
   - አዲስ የሚከፈቱና መደበኛ ፕሮግራም ወጥቶላቸው መሸፈን የማይችሉ መስመሮችን ተደራሽ ስለማድረግ
   - በሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ስለሚሳፈሩ ተጓጐች

- ልዩ ድጋፍ ስለሚያስፈልጋቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች

5) ክፍል አምስት - የአደረጃጀት እና የሀብት ሽግግር ሂደት አፈጻጸም
   - የአደረጃጀት የሽግግር ሂደት አፈጻጸም
   - የማህበራት የሀብት ሽግግር ሂደት አፈጻጸም
6) ክፍል ስድስት - ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
   - የቅሬታ አቀራረብ ስነ ስርዓት
   - የአሠራር እና የሥነ ምግባር ጉድለት የቅጣት አወሳሰን
   - የህዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች የቅጣት እርከን

6. <u>በመመሪያው ዋና ዋና የተገለጹ መስፈርቶች</u>

- የኦፕሬተሩ ቋሚ ቢሮ (የኪራይ ውል ወይም ካርታ)
- ለደረጃው የተቀመጠ የሰው ኃይል ቅጥር (የትምህርት ማስረጃና መሰል መረጃዎች)
- ለደረጃው የተቀመጠ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ብዛት (ሊብሬና መሰል መረጃዎች)
- ለደረጃው የተቀመጠ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ዕድሜ
- ለደረጃው የተቀመጠ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም
- ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ወቅታዊ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራ የምስክር ወረቀት እና የተሽከርካሪ ኢንሹራንስ
- ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ጅፒኤስ የተገጠመ ስለመሆኑ ህጋዊ ፈቃድ ከተሰጠው ድርጅት የሚቀርብ መረጃ
- የትራንስፖርት ንግድ ፈቃድ
- ሁሉም ተሽከርካሪዎች የተሳፋሪ የደህንነት ቀበቶ እና በሌሎች ህጎች የተቀመጡ መስፈርቶችን ሊያሟሉ ይገባል፤

7. <u>በቴክኖሎጂ የተደገፈ የኦፕሬተር አደረጃጀት ስርዓት</u>

❖ "የተቀናጀ የህዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተር አስተዳደር ስርዓት" ማለት የኦፕሬተሮችን ዝርዝር፣ የምዝገባ እና የደረጃ አሰጣጥ ሁኔታ፣ የተሽከርካሪ እና የአሽከርካሪ ዝርዝር መረጃለመመዝገብ እና ለመቆጣጠር የሚያስችል የኤሌክትሮኒክስ ስርዓት የተደገፈ ነው፡፡

- በመመሪያው መሠረት የሚበለፅገው ሲስተም የኤክትሮኒክስ የክፍያ ስርዓት እንዲኖር የሚያስችል ቴክኖሎጂ ነው፤
- የስምሪት አሰጣጡንም በቴክኖሎጂ የተደገፈ የሚያደርግ ስርዓትን ያካተተ ነው፤
- ኦፕሬተር ሆኖ የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት በሚኒስቴሩ የተዘጋጀውን እና አገልግሎት እየተሰጠበት ያለውን ይህን ሲስተም በመጠቀም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን አሟልቶ ማቅረብ አለበት፣
- ይህ ሲስተም ባለጉዳዩ የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድም ሆነ መሰል አገልግሎቶችን (ድንበር መሻገሪያ ፈቃድ፣ የብቃት ማረጋገጫ መስጠት እና ማደስ ወዘተ . . .) አገልግሎት ለማግኘት በአካል መምጣት ሳይጠበቅበት አስፈላጊ ኦርጅናል መረጃዎችን ስካን እና አፕሎድ በማድረግ አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያደርግ ስርዓት ነው፡፡ አስፈላጊ የሆኑ የአገልግሎት ክፍያዎችንም በኤሌክትሮኒክስ ክፍያ ስርዓት (በቴሌ ብር) እንዲከፍል በማድረግ አገልግሎቱ ሙሉ በሙሉ ከንክኪና ከብልሹ አሠራር በጸዳ መልኩ የሚሰጥበት ሲስተም ነው፡፡ በአጠቃላይ ይህ ሲስተም የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ከመስጠት ጀምሮ ልዩ ልዩ የደብዳቤዎችን አስተዳደር እና አጠቃላይ የኦፕሬተሩን የጉዞ መርሀ ግብር በመከታተል ዘርፉን ለማዘመን የሚረዳ እና ወደ ስራ የተገባበት ሲስተም ነው፡፡

8. <u>በመመሪያው ላይ ተስተካክለው የተካተቱ ነጥቦች</u>

- በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 8(6) ላይ ከ3ቱ አደረጃጀቶች ውጭ በንግድ ሕጉ ላይ በተመለከቱት ሌሎች የድርጅት ዓይነቶች ለመደራጀት ሲጠየቅ ለአክሲዮን ማኅበር የተቀመጠውን መስፈርት እንዲያሟሉ መደረጉ የትራስፖርት ዘርፍ በአግባቡ ከማስተዳደር፣ ከመምራት፣ ከመቆጣጠር አኳያ እጅግ ውስብስብ እና አስቸጋሪ በመሆኑ ሰብሰብ አድርጎ ለመምራትና ለመቆጣጠር እንዲያስችል ታስቦ ነው፡፡ ለመነሻነትም፡- መመሪያውን ለማሻሻል በተደረጉት ሁለት ጥናቶችን መሠረት ያደረገና ከውጭ ሀገራት ተሞክሮ፣ እንዲሁም ከዚህ ቀደም ሲል ሥራ ላይ የዋለውን የጭነት ትራንስፖርት የኦፕሬተር አደረጃጀት መመሪያን መነሻ በማድረግ ነው፡፡
- በረቂቅ መመሪያው ከአንቀጽ 10 ጀምሮ በየአደረጃጀቱ የተሸከርካሪ ብዛት እንደ አንድ መስፈርት ሲወሰድ የተሸከርካሪ ዕድሜን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ልዩ የሕዝብ ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር 15 ተሸከርካሪዎችን ማቅረብ የሚጠበቅበት ሲሆን የተሸከርካሪዎቹ ዕድሜ ደግሞ 7 ዓመት ነው፤ ከዚህም በተጨማሪ በየዓመቱ

አዳዲስ ተሽከርካሪዎችን እየገዙ ከስር ከስር እንዲተኩ ይጠበቃል፡፡ ተሽከርካሪዎቹ ዕድሜያቸው ከ12 ዓመት ከሞላ ልዩ መባላቸው ቀርቶ ወደ ደረጃ 1 ይሸጋገራሉ ማለት ነው፡፡ ሌሎቹም አደረጃጀቶች በዚህ እሳቤ የተደራጁ ናቸው፡፡ የአክሲዮን ማኅበር የተሽከርካሪ ብዛት ከፍ የሚል ሲሆን የኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በግማሽ ያንሳ፣ የግል ትራንስፖርትም ኃላፊነቱ ከተወሰነ የግል ማኅበር የተሽከርካሪ ብዛቱ ዝቅ ይላል፡፡ ምክንያቱም ከላይ እንደተመለከተው እንደቅደም ተከተላቸው በአቅም ደረጃ እኩል አይደሉም ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ በተጨማሪም ከዚህ ቀደም ወደ ዘርፉ ለመግባት የተቀመጠው የተሽከርካሪ ብዛት ከፍ ያለ በመሆኑ ወደ ዘርፉ የሚገቡ ባለሀብቶችን የማያበረታታ ስለሆነ በዚህ መመሪያ ቁጥሩ ዝቅ እንዲል ተደርጓል፡፡

- መመሪያውን ለማሻሻል የተደረጉትን ሁለት ጥናቶች መሠረት ያደረገና ከውጭ ሀገራት ተሞክሮ የኦፕሬተር አደረጃጀቶችን በመውሰድ የተዘጋጀ መመሪያ ሲሆን ይኸውም በአክሲዮን ማኅበር እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አደረጃጀቶችን ለማበረታታት ታስቦ የተደገ ነው፤
- በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 24 ላይ የተመለከቱትን አነስተኛ እና መለስተኛ የሕዝብ ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች የሚያደራጁት በሚኒስቴር መ/ቤታችን ሳይሆን በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች በመሆኑ መስፈርቶቻቸውም የሚወሰነው ራሳቸው በሚያወጡት መመሪያ የሚወሰን በመሆኑ ነው፡፡እንዲሁም በመመሪያ የተጠቀሱበት ምክንያት ሚኒስቴር መ/ቤታችን ከሚያስተዳድራቸው የፌዴራል መናኸሪያዎች የሚሰጣቸው አገልግሎት በመኖሩ ምክንያት ነው፡፡
- በተሽከርካሪ ላይ የሚገጠመው መረጃ ሰጪ መሣሪያ ተጓዡ ወደ አውቶብሱ ሲገባ የገባበት አውቶብስ የሠሌዳ ቁጥር ወይም የጎን ቁጥር ስንት እንደሆነ መሣሪያው መረጃ ሊሰጠው ይችላል፤ ወይም ጉዞ ከጀመረ በኋላ አውቶብሱ የት እንደ ደረሰ መሣሪያው ድምፅ በማሰማት ወይም ምልክት በመስጠት መረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ለአብነት ያህል **የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት** ላይ የተገጠመ መሣሪያ በድምፅ እና በምስል ባቡሩ የት ቦታ እንደ ደረሰ ፣ተጓዡ ከአውቶብሱ ሲወርድ በየትኛው በር መውረድ እንዳለበት መረጃ ይሰጣል፡፡ስለሆነም እነዚህን የመሳሰሉትን ጉዳዮች በሚመለከት የሕዝብ ትራንስፖርት ላይ የሚሰማሩ ተሽከርካሪዎች መስፈርትን በሚመለከት ሚኒሰቴሩ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያም ተመልክቷል፡፡

- "ከማኅበር ወደ ንግድ የሚተላለፈውን ሀብትና ንብረት ለማኅበሩ አባላት በግል ማከፋፈል አይቻልም፡፡" የተባለበት መነሻ ምክንያት **የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር** 1274 **አንቀጽ** 11(6) ላይ ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 468/97 መሠረት የተመዘገቡ የትራንስፖርት ማኅበራት ሀብትና ንብረታቸውን ቀድሞ ከነበሩበት ማኅበር አዲስ ወደ ሚሸጋገሩበት የንግድ ድርጅት እንዲያስተላልፉ ስለሚፈቅድላቸው ነው፤ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ወደ ንግድ ማኅበርነት ሳይለወጥ የቸሮታ ጊዜው ያለፈበት ማኅበር ያፈራው ንብረት ላይ የፍትሐ ብሔር ድንጋጌ ተፈፃሚ እንደሚሆንበት የተመለከተ በመሆኑ የረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 37(3) ድንጋጌ ይህን መነሻ ያደረገ ነው፡፡
- በሥራ ላይ ባለው መመሪያ ቁጥር 676/2013 ላይ ሞተር እና ካምቢዮ ቀይሮ የሚቀርብ ኦፕሬተር እንደ አንድ ጠንካራ ጐን ተወስዶ ይበረታታ የነበረ ሲሆን ነገር ግን የአንድ ተሽከርካሪ ዕድሜ፣ የቴክኒክና አካላዊ ብቃቱ የሚታየው የሞተሩን እና የካምቢዮ መቀየር ላይ ብቻ ሳይወሰን የተሽከርካሪውን የሥሪት ዘመን መነሻ አድርጎ ከአገልግሎት ብዛት፣ ከብልሽት፣ ...ወዘተ የተሽከርካሪውን አጠቃላይ የአቋም ሁኔታን ጭምር ከግምት ውስጥ በማስገባት በመሆኑና ሞተር እና ካምቢዮ በመቀየሩ ብቻ ተሽከርካሪው ለተገልጋይ ምቹና የተሟላ ቁመና ይኖረዋል ተብሎ ስለማይታሰብ በሀገራችን በአሁኑ ሰዓት እየደረሰ ካለው የትራፊክ አደጋ አኳያ የሚበረታታ ባለመሆኑና ለተጓዥ ምቾት ያላቸው በርካታ ፋሲሊቲዎች የተሟሉላቸው አዳዲስ ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገራችን የሚገቡበትንም ሁኔታ ለማበረታታት ነው፡፡ ሆኖም ሞተር እና ካምቢዮ ቀይረው ለሚቀርቡ ኦፕሬተሮች የሚደረገው ማበረታቻ በአሠራር ማንዋል ላይ ቢቀመጥ የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ ከመመሪያው እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

9. <u>የቅጣት ሪከርድ አያያዝ ስርዓት</u>

- ❖ አጥፊ ኦፕሬተሮች በቅጣት ሪከርድ ሲስተም አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰድባቸው ሲሆን፤ ይህም ቅጣቶቹ እንደየ ክብደታቸው በእርከን ተከፋፍለው የተቀመጡ ናቸው፡፡

10.<u>የቅሬታ አቀራረብ ስነስርዓት</u>

- ❖ በአገልግሎት አሰጣጥ ወቅት ቅሬታ ያደረበት ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ማቅረብ የሚችልበት ግልጽ ሁኔታ በመመሪያው እንዲካተት ተደርጓል፡፡

11.<u>የአስተዳደራዊ ቅጣቶች</u>

ማንኛዉም የህዝብ ትራንስፖርት ድርጅት በመመሪያው ላይ በዝርዝር የተመላከቱትን ጥፋቶች ፈፅሞ ሲገኝ እንደየጥፋቱ ክብደት እና ድግግሞሽ የሚወሰን ሆኖ የፅሁፍ ማሰጠንቀቂያ ከመስጠት ጀምሮ ለድርጅቱ የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫን እስከመሰረዝ የሚደርስ አስተዳደራዊ እርምጃ እንደሚወሰድ በመመሪያው ላይ በዝርዝር ተመላክቷል።